የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23 Year No. 19
ADDIS ABABA 3rd March,2017

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፫፻፺፰/፪ሺ፱ ዓ.ም
የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................ገጽ ፱ሺ፭፻፴፯

**CONTENT**

Regulation No. 398/2017
Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers Regulation ……..................................................................page 9537

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፰/፪ሺ፱

**<u>የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፰/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>መቋቋም</u>**

፩/ የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

Council of Ministers Regulation No. 398/2017

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE FEDERAL HOUSING CORPORATION</u>**

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No.25/1992

1. **<u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Federal Housing Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 398/2017".

2. **<u>Establishment</u>**

1/ The Federal Housing Corporation (herein after the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No.25/1992.

፫. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማዎች**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩/ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቤቶችን መገንባት፣ ማስገንባት፣ ማከራየት፣ መሸጥ እንዲሁም በተለየ ሁኔታ ሲወሰን መግዛት፤

፪/ የፌደራል መንግሥት በባለቤትነት የያዛቸውን ቤቶችና ይዞታዎች ማስተዳደር፣ ማከራየት፤

፫/ ለፌደራል መንግሥት ቤቶችና ሕንፃዎች አስፈላጊውን ጥገናና ዕድሳት በማድረግ የመጠበቅና የመንከባከብ፤

፬/ የፌደራል መንግሥት ንብረት የሆኑትን ቤቶችና ይዞታዎች በሕግ አግባብ መመዝገባቸውንና መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤

፭/ የፌደራል መንግሥት ቤቶችን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል ዘመናዊ የቤት አስተዳደር ሥርዓትን በመዘርጋት ሥራ ላይ ማዋል፤

፮/ በመንግሥት ቤቶችና ይዞታዎች ላይ የሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን መከላከል፣ የመንግሥትን ጥቅም ማስከበር እና አስፈላጊ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ፤

፯/ መንግሥት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግ ሥት ወጪ ተሸፍነው ለመንግሥት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት መገንባት፣ ማከራየት እና ማስተዳደር፤

3. **Supervising Authority**

The body to be designated by Government shall be the supervising authority of the Corporation.

4. **Head Office**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. **Purposes**

The purposes for which the Corporation is established are:

1/ to construct, cause to contract, rent out, sell or buy up on special decision houses that may be used for different services;

2/ to administer and rent out federal government owned houses and possessions;

3/ to carry out necessary maintenance and repair works to preserve and protect government owned houses;

4/ to make sure that the government owned houses and possessions are legally registered and protected;

5/ to devise modern management systems which enables effective administration of federal government houses and implement same;

6/ to prevent illegal action against government owned houses and possessions to ensure the interest of Government and take all necessary lawful measures;

7/ to construct and rent out houses for Government officials and employees; in accordance with government direction and budget out lays;

www.chilot.me

፰/ ለሚያስተዳድራቸው ቤቶችና ይዞታዎች የኪራይ ተመን ጥናት ማካሄድና ተግባራዊ ማድረግ፤

፱/ በሽያጭ እንዲተላለፉ በመንግሥት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ቤቶች ዋጋ አተማመን ጥናት ማካሄድ፣ ሲወሰን በውሳኔው መሠረት መፈፀምና የሽያጭ ገቢ መሰብሰብ፤

፲/ ለአስተዳደር አመቺ ያልሆኑ፤ መልሶ ለማልማት የማያስችሉና ኪራያቸው አነስተኛ የሆኑት ቤቶችንና ይዞታዎችን በመንግሥት ውሳኔ ማስተላለፍ፤

፲፩/ ለተወረሱ ቤቶች የቀድሞ ባለንብረቶች በሕጉ መሠረት አበል መክፈል፤

፲፪/ ከቤት አስተዳደርና ልማት ጋር የተያያዙ ጥናቶችን በማካሄድ በመንግሥት ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፫/ ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመስረት በሀገር ውስጥ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የሰው ሀይል፣ የፋይናንስና የዘመናዊ አስተዳደር ግብአቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

## ፮. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፴፫ ቢሊዮን ፻፵፬ ሚሊዮን ፯፻፸፪ ሺ ፻፴፮ (ሰላሳ ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሁለት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር ፲፩ ቢሊዮን ፵፰ ሚሊዮን ፪፻፶፯ ሺ ፫፻፸፰ (አስራ አንድ ቢሊዮን አርባ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰባ

8/ to study and implement the rental rate of houses and possessions under its control;

9/ to undertake studies on the valuation relating to government houses which the Government has decided to sell and collect proceedings there from;

10/ to transfer houses and possessions which are not convenient for administration, re-development and have least rental incomes, up on Government decision;

11/ to pay allowance to former owners of nationalized houses in accordance with the law;

12/ to conduct and implement researches related with house administration and development, up on approval by the Government;

13/ to make studies and forward proposals to get financial, technological and modern administrative inputs to be competitive and profitable at domestic level based on the directions given by the Supervising Authorities;

14/ to undertake any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

## 6. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Corporation is Birr 33,144,772,136.00 (Thirty Three Billion One Hundred Forty Four Million Seven Hundred Seventy Two Thousand and One Hundred Thirty Six Birr) of which Birr 11,048,257,378.**00** (Eleven Billion Forty Eight Million Two Hundred Fifty Seven Thousand and Three Hundred Seventy Eight Birr) is paid up in cash and in kind.

www.chilot.me

ስምንት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፱ሺ፭፻፵

፯. **ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. **ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. **የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር ፭፻፶፭/፪ሺ ተቋቁሞ የነበረው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

፲. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

7. **Liability**

The Corporation shall not be held liable beyond its total assets.

8. **Duration of the Corporation**

The Corporation is established for an indefinite duration.

9. **Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Agency for Government Houses established under Proclamation No.555/2007 are hereby transferred to the Corporation.

10. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negara Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of March, 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me